# አፍ (አ አዳም)
ትግስት ሳሙኤል

በእኔ አመለካከት ይህ የአዳም 'አፍ' የተሰኘው መጽሐፍ በመኖርና ባለመኖር፣ በማግኘትና በማጣት ላይ የሚያውጠነጥን፣ የቅልልቦሽ ጨዋታን ተምሳሌት በማድረግ ሰዎች በሕይወታቸው የሚያደርጉት ጉዞ ከሞት በኋላ እንኳን አላቂ እንዳልሆነ የሚያሳይ፣ በሜታፎር የነጠረ እና የአጻጻፍ ውበቱ ተወዳዳሪ የሌለው መጽሐፍ ነው።

ምንም እንኳን ሰፋ አድርጌ ስለ ድርሰቱ ቅርጽ ባልተነትንም አዳም ግን በገጽ 251 ላይ ‹የድርሰቱ ቅርጽ የተቀዳው ከባለ አምስት ጠጠር ቅልልቦሽ ጨዋታ ነው› ይለናል።

"ጨዋታው ሲጀመር አምስት ጠጠሮች ወለልታ ቦታ ላይ በ'ጉች' ይቀመጣሉ፡፡ ከነዚህ ጠጠሮች ቀልባችን ያረፈባትን ወይም ለመያዝ የምትመቸንን አንድዋን እናነሳታለን፡፡ ይህቺ' መቅለቢያ' ትባላለች፡፡ እንዲህ ስናደርግ 'ወለል' ላይ አራት ይቀሩናል፡፡ ቀጥሎ በእጃችን የያዝናትን መቅለቢያ ጠጠር ወደላይ አጉነን ከጎነችበት ወርዳ የዘረጋንላት እጃችን/መዳፋችን/ ውስጥ ከመግባቷ በፊት 'መሬት' ላይ ካሉት ጠጠሮች አንድዋን በፍጥነት በዛው የመጀመሪያዋን በወረወርንበት እጃችን እናነሳለን፡፡ በዚህ ዓይነት ተራ በተራ አራቱንም ጠጠሮች እንለቅማለን፡፡ (በዚህ ሂደት ውስጥ በመጀመሪያ ላይ 'መቅለቢያ' ብለን ያነሳናት ጠጠር 'መቅለቢያነቷ'ን ልታጣ ትችላለች) ቀለባው ሲያልቅ በእጃችን ውስጥ አምስት ጠጠሮች ይኖሩናል፡፡ በዚህ የመቅለብ ሂደት ውስጥ መቅለቢያችን ወይም የምንቀልባት ጠጠር ከእጃችን አምልጣ ከወደቀች እንደ ተሸናፊ እንቆጠርና ተራው ለተፎካካሪያችን ይተላለፋል፡፡ ይሄ አንድ ጨዋታ ነው።" ገጽ 251

መጽሐፉ ሲጀምር አዳም ዓይናችን በተለምዶ የሚያውቀውን ዓለም ያሳየናል። እዚህ ዓለም ውስጥ ደሞ እኛን የመሳሰሉ ሰዎች በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ከሌላው ሰው ያልተለየ ሕይወታቸውን ሲኖሩ ያሳየናል። የመጽሐፉ ጭብጥ ከ'አፍ' ጋር ስለሚተሳሰር ነገሩን አቅልለን የተለመደ የሕይወት ታሪክ እንጠብቃለን። ነገር ግን የመጽሐፉን ገጽ በገለጥን ቁጥር አዳም የገጸ ባሕሪያቱን አፍ እንደ በር ተጠቅሞ አይተን የማናውቀው ዓለም ውስጥ ይዘፍቀናል። አዳም uses አፍ not just as a physical space but as a gateway to deeper, often painful truths of the human experience.

በእያንዳንዱ ገጸ-ባሕሪ አፍ ውስጥ እየዋኘን የማጣትን፣ የምኞትን፣ የኃዘንን፣ የጸጸትን፣ የስደትን፣ የናፍቆትን፣ የማፍቀር እና ያለመፈቀርን ሲቃ አብረን እንቀምሳለን። አዳም፣ ‹ለካስ የሕይወትን ቀለማት አፍ በሚባለው በር ውስጥ ገብቶ ማየት ይቻላል እና ያ ደሞ extraordinary ክስተት ነው› እንድንል ያደርገናል።
አዳም ከሰውነታችን ይህችን የፊታችን ማዕከል ላይ የምትገኘውን አካል ወስዶ ለምን አፍተለተለው? አፍን በጣም የተለየ የሚያደርገው ምንድነው?

ሕጻን ልጅ ሲወለድ ዐይኑን ስለገለጠ በሕይወት እንዳለ ማረጋገጫ አይሆንም፤ ነገር ግን ዶክተሮች ጀርባውን መታ መታ አድርገው ማልቀስ ሲጀምር ወላዷ እርፍ ትላለች። ወደ መንፈሳዊው ዓለም ስንመጣ እግዚያርም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው። ነገር ግን እግዚያር ከአፉ የሕይወት እስትንፋስ እፍ እስኪልበት ሰው ሕይወት አልነበረውም። በአፍ እንበላለን፣ እንተነፍሳለን፣ ምላሳችንን ለበጎም ለክፉም ተጠቅመን እናወራለን። ነገር ግን ማውራት ብቻም ሳይሆን በፈጠርነው ቋንቋ ከሌሎች ጋርም እንግባባለን፤ እንስዳደባለን፤ እንማማራለን። ከአፍ የወጣ ቃል ጉልበት እንዳለው ስለሚገባን እንዳንረገም እንፈራለን፤ ሲመርቁን ደሞ አሜን እንላለን። በአፋችን እንጮኻለን፣ እንዘፍናለን። ሕመምንም በማቃሰት፣ ደስታችንንም በመሳቅ እንገልጻለን። ስንሞትም ውስጣችን የነበረው የሕይወት እስትንፋስ መውጫው አፍ ነው። አገርን ለመንገባት የሚያስችል ጉልበት የተገኘው ከአፍ ወደ አፍ እየተወራረደ የመጣ ታሪክ በጽሑፍ በመስፈሩ ነው። ፍቅራችንን ከናፍርትን በመሳም እንገልጻለን። እናም since mouth is an erogenous zone ወደ ሩካቤ ሥጋ የሚመራ የመራቢያ መንገድ ነው ልንለውም እንችላለን። አፍ ራስንም ለማጥፋት የምንጠቀምበት መሣሪያ ነው። ለሰውነት ጎጂ የሆኑ ነገሮችን መውሰድ፣ ከመጠን ያለፈ መጠጣት እና መብላት ከበሽታ አልፎ ሕይወትን የማሳጣት ኃይል አለው። አፍ ሲዘጋ እንኳን የራሱ መልእክት አለው። አባቶቻችን "ዝምታ ወርቅ ነው!" … "ዝም አይነቅዝም!" ብለው ሲተርቱ፣ ጊዜውን አውቆ የተዘጋ አፍ ጥቅሙ የትየለሌ እንደሆነ ለማሳየት ነው። አንዳንዴ ደሞ ጥልቅ ኃዘንን እና ድባቴን ከዝምታ በላይ አጉልቶ የሚገልጸው የለም።

አዳም እዚህ መጽሐፍ ላይ የተገለጹትን እያንዳንዱን ገጸ-ባሕሪያት የሚያስተዋውቀን የአፋቸውን በር ገርበብ አድርጎ በመክፈት ነው።

በጣም ባሳዘነቸኝ፣ በዋናዋ ገጸ ባሕሪ፣ በጌርሳሞት ልጀምር።

የጌርሳሞት እናት መግደላዊት

የጌርሳሞት እናት መግደላዊት፣ 'ማኅሌት' ከተባለው መጽሐፍ የተጸነሰች፣ የነፍሰ ገዳይዋ ሰላማዊት እና የጳውሎስ ልጅ ናት። (ህዳግ ገጽ 247-249) የጌርሳሞት እናት መግደላዊት አስተዳደጓ ከልጅነቷ ጀምሮ በቤተሰብ የተገፋች እና ያደገችበት ማኅበረሰብ ያቆሰላት ናት፤ Since she is the product of a highly dysfunctional family, (ህዳግ ገጽ 34-35) የጌርሳሞትን አባት ኮላሴን ከመተዋወቋ በፊት በልጅነቷ የተደፈረች፣ የእናትና የአባት ፍቅር ሳታገኝ ያደገች፣ ዲቃላ የወለደች፣ ከመጠን ያለፈ በመጠጣት ራሷን ስታ በተደጋጋሚ ማንነቷን ያረከሰች …ሰካራም ነበረች። (ገጽ 25, ህዳግ 34 35-36)

አዳም የጌርሳሞት እናት መግደላዊትን እና የአባቷ የኮላሴን የመጀመርያ ግንኙነት እንዲህ ገልጾታል።
"ከኮላሴ ጋር የተገናኘችው ለሥራ ጉዳይ ሰበታ አካባቢ ሄዳ ነው:: አንድ ቀን ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ዛፍ ሥር ከተከለችው ድንኳኗ ውስጥ ተኝታ ስትባንን ኮረብታ የሚያክል፣ ሦስት አራተኛ ገላው በፀጉር የተሸፈነ ሰውዬ ጎኗ ተኝቶ አገኘች፡፡ አስቀያሚነቱ አስደንግጦ ሳያሮጣት በፊት እንዳትጮኽ አፏን ይዞ አወቃት፡፡ የሥራ ባልደረቦቿ እዛው አካባቢ በየድንኳናቸው አድረው የነበሩት ከተኙበት ተነስተው ቁርስዋን እንድትበላ ጠሯት፡ መግዲ! መግዲ! መግዲ! ሲጠሯት ብትሰማቸውም ከላይዋ ላይ ሆኖ የሴትነት ጥልቅ ምሥጢር ከሚያሳያት ከአቶ ኮላሴ ገላ መላቀቅ አልፈለገችም፡፡ እኩለ ቀን ላይ ይሄ ሰው ከድንኩዋኑ ሲወጣ የሥራ ባልደረቦቿ ግራ ተጋብተው: ማነህ አንተ? የታለች መግደላዊት? አሉት:: ይህቺትና ብሎ እንደ ክር የቀጠነች፣ ላብ እንደ ቅባት ከላይዋ የሚወርድ፣ አፏ እንደ በር የተከፈተ፣ ዓይኖቿ ግንባሯ ውስጥ የተሰነቀሩ መግደላዊትን ክንዱ ላይ ተጋድማ አሳያቸው::" ገጽ 25-26 ህዳግ)

ድርሰቱ ኮላሴ የመግደላዊትን አፍ 'የሸፈነው' የራሱ አስቀያሚ ፊት አስፈርቷት እንዳትሮጥ በመፍራት ነው ይለናል። ሆኖም ግን እኔ የመግደላዊት አፍ የመያዝ ምክኒያት ሌላ ትርጉም አለው ብዬ እጠረጥራለሁ። የመግደላዊት አፍ የውድቀቷ ምልክት ነበር። ራሷን ለመርሳት የጠጣችው በአፏ ነው። ለማስታወስ የማትችላቸውን ወንዶች ጠርታ የጋበዘችው/የሳመችው በከንፈሯ ነው። ንግግሯ የደበዘዘው፣ ሳቋ ባዶ የሆነው፣ ማንነቷ የጠለሸው በአፏ ባስገባችው መጠጥ ምክንያት ነው። አፏ ወደ ትርምስ መራት፤ በመጨረሻም፣ ከጸጸት ጋር በጣም የተቆራኘው አካል ሆነ። (ገጽ 25) ኮላሴ፣ በአንድ ወቅት የሁከት፣ የመጠጥ፣ የስካር፣ የመርሳት፣ የመጸጸት ተምሳሌት የነበረው የመግደላዊትን አፍ ይዞ/ዘግቶ/አፍኖ 'አወቃት' ሲል ምን ለማስተላለፍ ፈልጎ ይሆን?

በእኔ አመለካከት ይህ ተራ፣ ስሜታዊና ጊዜያዊ ሩካቤ አይመስለኝም። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መልኩ፣ አንድን ሰው"ማወቅ" ሥጋዊ ብቻ አይደለም - ቅርበት ያለው፣ የተሟላ እና ለውጥ የሚያመጣ ግንኙነት ነው። ብዙ ግዜ 'አወቃት' የሚለው ቃል አገባት ወይም የራሱ አደረጋት ከሚል ሐሳብ ጋር የተያያዘነው። የአካል አንድነትን ብቻ ሳይሆን ያንን ሰው በጥልቅ ለማወቅ መጓጓት እና ኅብረቱንም ዘላለማዊ ለማድረግ ነው። ኮላሴም ይህንኑ ነው ያደረገው።

"ስሙን ብቻ ነግሯት ከሰበታ አካባቢ በመሥሪያ ቤት መኪናው ጭኖ ወጨጫ ተራራ ግርጌ ታቦት ማደሪያ ቤቱ ይዟት መጣ።" ህዳግ ገጽ 34

መጋረጃውን ከፍቶ በተከሻው ላይ ያለምንም ኀፍረት ተኝታ ሲያሳያት፣ አፏ በትንሹ ተከፍቶ ነበር። ክፍተቱ እንደ ድሮ ወይነጠጅን ለማንቆርቆር ሳይሆን በአንድ ወቅት የትርምስ መሣሪያ የነበረው ያ አፍ በአንድ በመወሰኑ የተሰማትን እርካታና እረፍት ለመግለጽ ይመስለኛል። መግደላዊት ከዚያን ቀን ጀምሮ ዳግመኛ ጠጥታ አታውቅም። ራሷን ለሌላ ወንድ አሳልፋ ሰጥታ አታውቅም። የኮላሴ ሚስት እና የጌርሳሞት እናት የሆነችው ኮላሴ በዚህ መልኩ ካወቃት በኋላ ነው። (ገጽ 28 ይነበብ)

"ስካር ስትደጋግም ገንዘብ እያነሳት ጋባዥ ፈለገች፡፡ ጋባዥዋም በመልሱ እሷን ፈለገ፡፡ የስብዕናዋን ምድር ምሳ የምትጠጣ የጥፋት ሞተር የጫነች ወይዘሪት ሆነች፡፡ ለአንጓጣጧትም በግድየለሽነት እግሯን አነሳች፡፡ የማኅፀንዋ ምጣድ ላይ ሊጡን ያላዞረ ማነው? (አእምሮዋን የምትጠቀም ጠንቃቃ መሆኗ አልቆ ግድየለሽ የሆነችበት የጊዜ ወሰን የትና መቼ ጋ እንደሚጀምር ሁልጊዜ ይሳታታል) ኅብረተሰቧ በአሉባልታው እንደፈጠራት ሲገባት ብልጠቱን ፈራችው:: መሸሽና መደበቅ ፈለገች፡፡ መሸሺያና መደበቂያ ግን አልነበረም፡፡ ኮላሴ አንድ ቀን መጣ፡፡ አያት፡፡ አብሮአት አመሸ፡፡ ወደዳት፡፡ አወቃት፡፡ የሰደባትን ያዋረዳትን ዓለም ሰብሮ ድንኳን ሆናት፡፡ ባትፈልግም የገላመጥዋትን መልሳ ገላምጣ ማደር ቻለች፡፡ እሷ ላይ አፉን ለስድብና ለሽሙጥ የከፈተ ለዘላለም ይዘጋበታል፡፡መግደላዊትን አናውቅሽምና ነው፤ የሆነ አውሬ የመሰለ ባል አገባሽና መፎለልሽ ነው? ያሉዋት ሁለት ሰዎች ዛሬ ድረስ ያለመንገጭላ ለሃጫቸውን እያዝረበረቡ ይሄዳሉ፡፡" -ህዳግ ገጽ35

የጌርሳሞት አባት ኮላሴ (magical realism and synchronicity 1)

አዳም ስለ ጌርሳሞት አባት፣ ስለ ኮላሴ ማውራት ሲጀምር that is when he started adding the 'fantastical' into this realistic fiction. ስለ ኮላሴ ማንበብ ስንጀምር የመጀመሪያ የሚቆሰቆስብን ጥያቄ ኮላሴ ማን ነው ሳይሆን ኮላሴ ምንድነው? የሚለውነው። ህዳግ ገጽ 23-24 እንደሚገልጸው ኮላሴ ዝንጀሮዎች የሚራወጡበት የካባ ገደል ሥር ወድቆ የተገኘው በሕጻነቱ ነው። አሳዳጊው አቶ ባሪያው ሲያገኙት ከፊቱ በስተቀር ገላው በፍዝ ቡናማ ፀጉር የተሸፈነ ሲሆን በደንብ ሊያዩት አቶ ባርያው ወደ ፊቱ ሲጠጉ እንዲያቅፉት ፈልጎ

የዘረጋው እጆቹ በስስ ፀጉር የተሸፈኑ ነበሩ። ኮላሴ ለአቅመ አዳም ደርሶ መግደላዊትን አግብቶ የጌርሳሞት አባት ተብሎ የሚጠራ 'ሰው' ቢመስልም According to Adam ኮላሴ is a human with an ape value or sensibility. … አዳም ይህ ሰው በእርግጥም ዝንጀሮ ነው ብለን እንድናስብ ብዙ ብዙ ምልክቶችን ሰጥቶናል። (ህዳግ ገጽ 23-33)

ጎበጥ ያለ ገጽታው፣ በጸጉር የተሸፈነ ሰውነቱ፣ የፊቱ ማስቀየም፣ ክንዶቹ ረጃጅም መሆናቸው፣ አበላሉና የምግብ ምርጫዎቹ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ችግሮችን በመደባደብ እና በዓመፅ ለመፍታት መሞከሩ እና የልጁን የማፍቀር እና የመፈቀር ነጻነት በፍጹም ጭፍንነት ማፈኑ ‹ይህ ሰው እውነትም ሰው ሳይሆን 97 ፐርሰንት ዘረመላቸው ከኛ ጋር የሚጋሩንን ዝንጀሮዎች ይመስላል› እንድንል ያደርገናል።

ኮላሴ በሚያደርጋቸው ነገሮች ውስጥ ሁሉ ምክኒያታዊነትና ጥልቅ አስተሳሰብ የለም። ቋሚ የሚደግፈው የእግር ኳስ ቡድን ሳይኖረው በየጊዜው ስቴዲዮም እየሄደ በመደባደብ ጊዜውን ያሳልፋል። (ህዳግ ገጽ 31)

ነገር ግን ከሁሉ በላይ ዝንጀሮነቱን የደመቀ ህትመት ሰጥቶ እውነትም ዝንጀሮ ነው እንድል የሚያደርገን ኮላሴ በየሁለት ሳምንቱ ከልጅነቱ ጀምሮ ሲያይ የነበረው 'የገደል ሕልም' ብሎ የሰየመው ሕልሙ ነው። ህዳግ ገጽ 32-33

ኮላሴ ሰዎች በተለምዶ እንደሚያልሙት ሰውኛ ሕልም አያልምም። He dreams places and things that are deeply buried in his subconscious. የሚያውቀውን ገደል ያልማል። ስለ ዝንጀሮ ዘመዶቹ ያልማል። ራሱን በፍትወት ሲቃጠል ያልማል። በሕልሙ የምታማልለው ግን መግደላዊት ሚስቱ ወይም ሌላ ቆንጆ ኮረዳ ሳትሆን የዝንጀሪት ጥቅሻ ናት። ኮላሴ ከዚህች ዝንጀሮ ጋር ፍቅር ሲሠራ ያያል።

"ከመሃል እንስቲቷ ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ እየዘለለች ወደ እሱ መጣችና ከእሱ ሳትርቅ ቆም ብላ ግራና ቀኝ እየዞረች የቂጥዋን የበሰለ መላጣ አሳየችው፡፡ የዝንጀሪት ጥቅሻ አማለለው፡፡ ….አንድ ጊዜ እመር ብሎ ዘለለና እንስቲቱ አጠገብ ቅርንጫፍ ላይ ጠብ አለ፡፡ እንስቷ እንደ ኮሸሽላ ትሸታለች፡፡ እንደ ጦስኝም ትሸታለች፡፡ በአፏ አፉን ታከከችውና ከጎኑ ተንበለበለች፡፡ ከኋላዋ በፍጥነት ወጥቶ መነቃነቅ እንደ ጀመረ ከየት እንደመጣ ያልገባው ጥፍራም ጥፊ አፉ ላይ አረፈ፡፡ ደኑ በዝንጀሮ ጩኸት ታመሰ፡፡" ህዳግ ገጽ 33

እንደ ሌሎቹ ገጸ-ባሕሪያት የኮላሴን 'አፍ' ገርበብ አድርገን ስንገባ አንድ ጥልቅ ነገር እንገነዘባለን። ዝንጀሮ እንደሆነ የሚጠቁሙ ምልክቶች ቢኖሩም ኮላሴ ሙሉ ለሙሉ የሰው ስብዕናን ለብሶ ከሰዎች ጋር ተቀላቅሎ እንዲኖር የረዳው አፉ ነው። መግባቢያ ቋንቋ ማወቁ ነው። አስተሳሰቡ የዝንጀሮ ቢሆንም በቋንቋ መግባባት መቻሉ የአፍን ጉልበት አዳም

በሚታፎር እያሳየን ይመስለኛል። ይህንን እንድል ያደረገኝ ነገር ገጽ 225-227 ላይ ኮላሴ ወደ ሙሉ ዝንጀሮነት ሲለወጥ እናያለን። በዚህ ሂደት ውስጥ ራሱን በቋንቋ ለመግለጽ አፉን ከፍቶ ሲታገል ግን ሲያቅተው እናስተውላለን። የሚወዳቸው ሚስቱን እና ልጁን ስማቸውን ለመጥራት ሲታገል ስናየው፣ በዝንጀሮና በሰው መሃል ያለው ቀጭን መስመር ደብዛዛ ቢመስልም ነገር ግን ዝንጀሮ የመናገር ችሎታውን ሲቀማ እና ከሰው መግባቢያ ቋንቋውን (አፉን) ሲነጠቅ መስመሩ ኃይሉ ጎልብቶ ከሚገባው በላይ ይደምቃል።

“የቀረ ጨርቁን ሁለቱም ተረዳድተው እያሽካኩ ከላዩ እየቀዳደዱ ጣሉት፡፡ ዝንጀሪትን እንደ አቀፈ ለአፍታ ወደመጣበት አቅጣጫ አየ፡፡ በትላልቅ ዛፎች መሃል ሰዎች ያያል፡፡ መኪናውን ያያል፡፡ መኪናዋን የማያውቃት፣ አጠገቧ ያሉትም ልጆች አደገኛ መሰሉት፡፡ ዝንጀሪት በኩራት ዞረችውና አጉተመተመች፡ የተለየህ ባቡን ነህ፡ ከሚሊዮን ዝንጀሮዎች ቢያንስ በአንዱ ውስጥ ሰው እንደሚኖር፣ ከሚሊዮን ሰዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ ዝንጀሮ እንደሚኖር የሚገባው እሱ ብቻነው:: ሴቲቱን በቀኝ እጁ ስቦ ጉያው ከተታት፡ አዳምና ሔዋንን መሰሉ፡፡ ደረቱን ተደግፋ ቀና ብላ እያየችው አዛጋች፡፡ ከተከፈተ አፏ የሳር፣ የሽንት፣ የኮሸሽላና የጦስኝ ማራኪ ጠረን ሸተተው፡፡ ከንፈሮቹ ደርቀው ሊጠራው ያልቻለ እውስጡ የሚያስገመግም "*መግደላዊት መ መ መመመ መመመመ ! መ! ሁ!ሁሀ!ሆሆሆ!* አናቱን ወደ ሰማይ ሰቅሎ፡ ደሞ “*ጌርሳሞት ? ! ገገ ! ገገገገ!ገገገገ!ገገ!ጋ!ጋጋ! ጋጋገ!!!* ወደ ገደሉ ፊቱን አዞሮ፡፡ እውነት ይሁን ውሸት አይገባውም፡፡” ገጽ 227

የኮላሴ ታሪክ ላይ ሙሉ ለሙሉ ወደ ዝንጀሮነት ከተቀየረ በኋላ ዋናውን ገመሬ (chief of the monkeys) ገድሎ ራሱ ያንን ስሥልጣን እንደ ያዘ እናያለን። ኮላሴ የሰው ሕይወቱን እየኖረ ሳለ ከሰዎች የተማረው ሌላውን ገድሎ ሥልጣን መቀማት ነው ብዬ አስቤ ነበር፤ ነገር ግን የአዳም መልስ ክትክት ብዬ እንድስቅ ነው ያደረገኝ። ዕድሜ-ልኩን ስቴዲየም እየተመላለሰ ሲደባደብ የኖረው ኮላሴ፣ (the human with the ape sensibility) ከሰዎች የወሰደው ጠቃሚ ትምህርት ምን ነበር? ስቴዲየም ሲመላለስ የተማረው፣ ሰው ቡጢ ሲሰነዝርበት ማጎንበስ እና በሾኬ ሰው ጠልፎ መጣል ነው። ኮላሴ ከገመሬው (chief of the monkeys) ጋር ሲደባደብ የምታሳየውን፣ ይህችን ከሥር ያለችውን አንቀጽ አንብባችሁ እስቲ እኔ እንደሳቅኩት እናንተም ሳቁ።

"ከሁዋላዋ ሊወጣ ሲል ሰፊ መዳፍ ወደ ፊቱ ሲሰነዘር አየ፡፡ የእንስቷን ዳሌ ሳይለቅ ቀልጠፍ ብሎ አጎነበሰ:: ገመሬው የሰደደው ጥፊ ጨርቃሙን ዝንጀሮ ስለሳተው በብስጭት ሊከመርበት እያጓራ ተጠጋው:: ጨርቃሙ ጋለል ብሎ በታኮ ጠለፈው:: ስታድዮም፡፡ ቃሉን በአፉ ሊጠራው አልቻለም፡፡ ከንፈሮቹ እምቢ አሉት፡ ቃሉ አእምሮው ውስጥ ይገላበጣል፡፡ ገመሬው የቆመበትን ዛፍ ስቶ ሊወድቅ ሲል አንድ ቅርንጫፍ ይዞ ተንጠልጥሎ ቀረ፡፡ ገመሬው ፊት ላይ ድንጋጤ፣ ፍርሃትና መገረም አሉ፡፡ በሾኬ ተጠልፎ አያውቅም።" ገጽ 227

**ጌርሳሞት (magical realism 2)**

እዚህ ድርሰት ውስጥ በአምስት ጠጠሮች የተመሰሉ ገጸ-ባሕሪያት አሉ፡፡ አራቱ ነጫጭ ሲሆኑ አንዷ ጥቁር ናት። ጥቁሯ እንደ ቋሚ ቀላቢ የተደረገችው ጨዋታው ሲጀመር በእጅ የምትያዘው ጌርሳሞት ስትሆን ነጮቹ ተቀላቢ ጠጠሮችን የሚወክሉት ጌርሳሞትን የተመኟት ዘሪሁን፣ ገለታ፣ ባካፋ እና አቡ(ራሚሱ) ናቸው:: ገጽ 40

አዳም የሁሉንም ገጸ ባሕሪያት ገጽታቸውን ሲገልጽ አፋቸው ላይ አተኩሯል። ጌርሳሞት በጣም የሚያምር ከንፈሯ አፏን አስውቦታል። ዘሪሁን ወሬ ይወዳል ግን የሚታወቀው በማፏጨት ክህሎቱ ነው። ገለታ በግራ ጉንጩ ላይ የሚያምር ስርጉድ (dimple) አለው። ዝምተኛ ቢኾንም፣ በይበልጥ የሚታወቀው ሲያንጎራጉር በሚያወጣው መሳጭ ድምጹ ነው።ባካፋ መሳቅ ይወዳል፤ ነገር ግን ከምንም በላይ የምግብ አፍቃሪ ነው። አቡ (ራሚሱ) በሁሉም ነገር ብስጩ ሲሆን ተረበኛ እና ምላሰኛ ነው።

ጌርሳሞት እዚህ ግቢ የማትባል መልኳ ብዙም የማያስጎበድድ ኮረዳ ነበረች። (ገጽ 40) የጌርሳሞት የአፍና የከንፈር ውበት የጀመረው ዕድሜ ለ-magical realism በአንድ በሚደንቅ ክስተት ምክኒያት ነው። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ከንፈሯ እያደር መዋቡን ቀጠለና የሷን አፍ አይቶ የማይፈዝ አልተገኘም። ክስተቱ ምንነበር?

ለበዓል የበግ ቆለጥ እንድትጠብስ ታዘዘች። ቆለጦቹ በእሳት እየጠየሙ ማበጥና ክርታሶቻቸው መሰንጠቅ ሲጀምሩ የሚሆነውን የበለጠ ቀርባ ለማየት ፊትዋን በጉጉት ወደ ምድጃው ስታስጠጋ አንዱ ወደ እስዋ በኩል ያለው ቆለጥ ድንገት ፈነዳና የሚያቃጥል ሞራ ተፈናጥሮ አፍዋ ላይ መታት። ገጽ 39

ከዚያን ጊዜ ወዲህ የጌርሳሞት አፍና ከንፈር በየቀኑ እያማረበት ሄዶ እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ጎረምሶች በየተራ ክፉኛ ተመኟት። የበግ ቆለጥ ፍንጣቂ የገባበት ከንፈር እያደር ማማሩ እና እነዚህን ጎረምሶች ወደ እሷ እንደ መግነጢስ መሳቡ ለምን ይሆን? በተለያዩ ባሕሎች ወንዶች ወንድነታቸው እንዲጎለብት፣ more masculine and fertile እዲሆኑ የበግ ቆለጥ እንዲመገቡ ይመከራሉ። ከበጉ ቆለጥ የተፈነጠቀው ሞራ ከንፈሯን ማስዋቡ እና ጎረምሶቹን ወደሷ መሳቡ feels like a metaphorical expression of her mouth being a powerful portal that invites the male fertile energy.

ንብ አበባን ለመቅሰም እንደምታንዣብበው ጌርሳሞትን የከበቧት አራት ጓደኛሞች ገለታ፣ ዘሪሁን፣ አቡ (ራሚሱ) እና ባካፋ ይባላሉ። እነዚህ ጎረምሶች በተለያዩ ጊዜያት በጌርሳሞት የአፍ ውበት ተስበው ፍቅራቸውን ለመግለጽ ያለሙ ነበሩ። ገለታ በስደት ከአገር በመጥፋቱ ጌርሳሞትን ለመተው ተገደደ። ዘሪሁንን የጌርሳሞት አባት ስለደበደበው ከአጠገቧ ጠፋ።

ጌርሳሞት ጥርሷ ላይ ብሬስ ከገባ በኋላ የአፏ ውበት በመደብዘዙ አቡና ባካፋ እርግፍ አድርገው ተዎት፤ ሸሿት። በስተመጨረሻ በብሬሱ ምክንያት አፏ ቆስሎ ፍቅር ተንኖባት እናያለን።

ጌርሳሞት ሁሉም የተመኟት ነገር ግን ማናቸውም ያላገኟት Utopia ነበረች። በምናባቸው ልዩ አድርገው የሳሏት፣ ጠንቅቀው ያላወቋት ግን አፏ በር ላይ ደጋግመው የሰገዱላት ናት። ይህቺ የፍጽምና ምልክት ጸጋዋ የማይደርስባት ሕልም ናት። በቅዠታቸው መሃል ብቻዋን የቆመች፣ በአባቷ አምባገነንነት አጥር ተከልላ ልባቸው ውስጥ የገዘፈች Utopia ናት።

ነገር ግን የጌርሳሞት ሕይወት በዚህ ያበቃል ማለት ዘበት ነው። ያለ አባቷ አምባገነናዊ አመራር ጌርሳሞት ሕይወቷ ሲቀጥል ምን ይገጥማት ይሆን? ነጻነቷ ምን ዓይነት ዕድል ይከፍትላት ይሆን? የማታውቃት አያቷ (ሰላማዊት) ሕይወትዋ ውስጥ በመምጣትዋ ምን ሊፈጠር ይችል ይሆን? በስተመጨረሻ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ልትሄድ ሻንጣዋን ስታስተካክል እናነባለን። እናስ እዛ ሐዋሳ ዕጣ ፈንታዋ ምን ይሆን? የትምህርት ዕድል አግኝታ ደቡብ አፍሪካ ብትሄድስ ማን ይከለክላታል?

## ገለታ እና ሰርጀንት ዴላኒ (Magical realism and synchronicity 3)

የገለታ የሕይወት ጉዞ ስላሳዘነኝ፣ ስለመሰጠኝ፣ በዋነኛነት የአዳም Magical Realism አጻጻፍ ገለታ ላይ በጣም ስለሚጎላ እና ስለሚያምር ገለታን ስቤ አውጥቼ የእሱ ሕይወት ላይ አውጠንጥኛለሁ።

መጽሐፉ በጥቅሉ የአዳምን የአጻጻፍ ስልት፣ የምናቡን ጥልቀት እና ስፋት፣ ፍርሃት የሌለበት አገላለጹ፣ የቃላት አጠቃቀምና ውበት፣ በአጠቃላይ የፈጠራውን ረቂቅነት ያሳያል። በተጨማሪ ለኔ የገለታን ታሪክ ልዩ የሚያደርገው የአዳምን ሆደ-ቡቡነትንም ስለሚያሳየኝ ነው። አዳም እዚህ ታሪክ ላይ ገለታን በመጠቀም በስደት ተንከራትተው፣ ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን ሳያውቁ፣ ስማቸው ሳይታወቅ፣ መድረሻቸው ሳይታወቅ እንዲሁ እንደ ዋዛ ሕይወታቸው በየቦታው ተቀጥፎ ወጥተው ለቀሩ ወጣቶች መታሰቢያ (narrative tribute) ማስቀመጥ የፈለገ ይመስለኛል። Adam is an empathic storyteller የምልበት ምክኒያት ይህ ጉዳይ የስንብት ቀለማት ላይም ስለገጠመኝ ነው። የስንብት ቀለማት ላይ ዘውዲት የተባለች እርጉዝ ወጣት ሴት ከገባችበት የከፋ መቀመቅ መውጫ የሚሆን መፍትሄ ስላጣች በአንድ የሆቴል አልቤርጎ ውስጥ የራሷን ሕይወት በገዛ እጇ እንዳጠፋች አንብበናል። ልክ እንደ ገለታ ታሪኩ የተጻፈበት መንገድ አንባቢው ውስጥ ስሜቱ እንዲጋባ ተደርጎ በጥልቅ ርኅራኄ የተጻፈ በዚህ መልኩ ሕይወታቸው ላለፈ ወጣቶች መታሰቢያ ሆኖ የቀረበ ይመስለኛል።

ገለታ የሚታወቀው ግራ ጉንጩ ላይ ባለው ዲምፐል ምክኒያት የተገናጸፈው ውበት እና በድምፁ ማማር ነው። ገጽ 10-13

አዳም ስለገለታ ዲምፐል ሰዎች ምን ይላሉ በማለት በህዳግ መልክ ሁለት ሙሉ ገጽ (11-12) ስለ ገለታ ዲምፐል ጽፏል። በእኔ አመለካከት የገለታ ዲምፐል የማንነቱ ማጠንጠኛ ስለሆነ አዳም አንባቢው የገለታ ዲምፐል ላይ እንዲያተኩር ሆን ብሎ ያስገባው የዲምፐል አሉባልታ ነው። የታቦት ማደሪያ ሰዎችን ‹ገለታ ማነው?› ብለን ብንጠይቅ ስለገለታ ከዲምፐሉ ባሻገር የሚያውቁት ነገር የለም።

"ገለታን ሰዎች ቢያውቁትም በትክክል አይረዱትም፡፡ እያዩ አያዩትም:: እሱን የሚያይ እንግዳ ሰው የሚያየው እንግዳ የሆነውን የገጹን ውበት ብቻ ነው::” ገጽ 14

ከጊዜ በኋላ ደሞ በማይታወቅ ምክንያት ዝምተኝነትን አብዝቶ እንደመረጠ እናቱ ያወራሉ። “የፈራሁት ግን ደረሰ መሰለኝ አድብቶ አድብቶ ከፍ ሲል ጋግርታም ሆነብኝ፡፡ ….ሁልጊዜ ግን እፀልይለታለሁ፡፡ ድሮ ከወዳጆቹ ጋር ሲንቀለቀል የማየው ልጅ አሁን አሁን እጆቹን ኪሱ ከቶ ሲያስብ አየዋለሁ፣ ወይም ሲያንጎራጉር እሰማዋለሁ፡፡” ህዳግ ገጽ 49

የገለታ አፍ ላይ ስናተኩር የዝምታው ግዙፍነት በድባቴ እንደሚሠቃይ ያሳብቃል።

"ገለታ ለምን ከሁሉ ራቅ ብሎ ይቀመጣል? አራራቁ ውስጥ ለምን በስሜት ብቻ የሚለካ የመሰለ ርቀት አለ? ከሁለት ወይም ከሦስት ዓመታት በፊት ቀልቃላ የነበረው ይሄ ልጅ ብርድ እንደተነፋበት ሁሉ ለምን ቀዘቀዘ? ….. አብሮ አደግ ጓደኞቹን ለምን እንደ ባዕድ አርቆ ያያቸዋል? አጋጣሚ ነው? አጋጣሚነቱ ለገለታ ነው ወይስ ለተመልካች? ተወልዶ ላደገበት፣ ለቦረቀበት ዕድሜው እዚህ ለደረሰበት ታቦት ማደሪያ እንዲህ ከሆነለአዲስአባ እንግዳ አይሆንም? ለአዲስአባ እንግዳ ከሆነ ለአገሪቷአይሆንም? ለአገሪቷ እንግዳ ከሆነ ለአፍሪካ አይሆንም? ለአፍሪካ እንግዳ ከሆነ ለዓለም አይሆንም? ለዓለም እንዲህ ከሆነ ለፍጥረታት እንግዳ አይሆንም? ለአምላክስ? በትክክል ግን ገለታ እዚህ ቦታ የለም። ስፍራ በገላ ብቻ ሳይሆን የሚሞላው በድምፅ ነው ይላሉ ሳይንቲስቶች፣ ጪሂዎች፣ ዘፋኞችና የለቅሶ መርዶነጋሪ ጥሩምበኞች፡፡ ማለት ዝምታ ቦታ እንደማይዝ ሁሉ። ከቀጭኔ የበለጠ ዝምተኛ አለ? በገላዋ የምትሸፍነው ቦታ ግን ከአራት ጅብ ይበልጣል፡፡" ገጽ 49

ገለታን ሌላ በጣም ያሠቃየው የነበረው ለአምስት ዓመታት ሙሉ ከጠዋቱ 1 ሰአት ተኩል የሚያልቀውን የማይገባውን ተደጋጋሚ ሕልም ማየቱ ነው። ሕልሙ ላይ በዓይኑ ሰው ባይታየውም የሰውዬው ድምፅ ግን "ዲድ ኤኒ በዲ ተች ዚስ ጋይ? (ይሄን ሰው የነካው አለ?) ይላል፡፡ ገጽ 54-55

ተደጋጋሚ፣ ተመሳሳይ ሰዓት (1.30) ላይ የሚያልቅ ሕልም (ዲድኤኒ በዲ ተች ዚስ ጋይ? (ይሄን ሰው የነካው አለ?)

ነገሮችን ለማሳጠር ገለታ ብዙም ሳይቆይ ቤተሰቡን እና ወዳጆቹን ሳያሳውቅ ከአገር ተሰድዶ ደቡብ አፍሪካ ይገባል። ስደት ላይ እያለም ይሞታል። አባትና እናቱም ሆነ የቅርብ ወዳጆቹ ገለታ የተሰደደበትን ሀገር አያውቁም ነበር።

አዳም ሕልምን mystical bridge በማድረግ ሁለት የተለያየ አገር ውስጥ የሚኖሩ የማይተዋወቁ ሰዎችን በሎጂክ ልናብራራው በማንችለው ሁኔታ አገናኝቶ let us see how he gently blurred the line between the surreal and the real.

ገለታ በሕይወት እያለ በሕልሙ ይሰማው የነበረው ድምፅ የደቡብ አፍሪካው ፖሊስ የሰርጆንት ዴላኒ ድምፅ መሆኑንየምንረዳው ዴላኒ የገለታ ሬሳ ዙሪያ የተሰበሰቡትን ሰዎች የጠየቃቸውን ጥያቄ ስንረዳ ነው።
ገለታ እና ዴላኒን የሚያመሳስላቸው ምንድነው? ሁለቱም ድባቴ ውስጥ ነበሩ።

ዴላኒ የሚታወቀው ከንፈሩ ላይ ባለው ጉድለት እና በቦርጫምነቱ ነው። (ገጽ 206-207)

ሕይወት ሰልችቶታል፣ ሚስቱ ከሰፈር ጎረምሶች ጋር ከመዳራት አልፋ ሌት ተቀን በጭቅጭቅ ትጠብሰዋለች፣ ጎረቤቶች ያሽምዋጥጡታል፣ ብዙ ቢለፋም ይህ ነው የሚባል ገንዘብ የለውም፣ ሕይወቱ በየቀኑ በሽብር እንደተሞላ ያስባል፣ ከሰዎች መሃል ከሚኖር ድንጋይ እየቆረጠመ በረሃ ቢሰደድ ይመርጣል፣ አሁኑኑ እንደ ተኛ ቢሞትም ቅር አይለውም.. 208

"እዚህ ዓለም ላይ መኖር አይፈልግም:: አንዳንዴ ከትዳሩ፣ከሥራው፣ ከሚበላውና ከሚጠጣው ብቻ ሳይሆን ከመፈጠሩ የተጣላ ይመስለዋል፡፡ ቢሆንም ራሱን አያጠፋም፡፡" 210

ዴላኒ ለምርመራ የገለታ ሬሳ ጋር ሲደርስ ይህን እናነባለን።

"ከጃኬት ኪሱ የፕላስቲክ ጓንት አውጥቶ እየለበሰ ወደ ሞተው ልጅ ቀረበ፡፡ ልጁ ያረጀ ሌቪስ ጃኬት ለብሷል፡፡ የቆሸሸ ካኪ ቦላሌ አድርጓል፡፡ ቀበቶው በቦታው ነው:: የቀበቶው ቆዳ እየተበላ ይሁን ልጁ እየከሳ፣ ሽበው የመጨረሻው ዐይን ውስጥ ነው:: ከመቆሸሽ በስተቀር ሱሪው ላይም ይሁን ጃኬቱ ላይ የደም ምልክት የለም፡፡ ደከሞት እዚህ ዛፍ ሥር መጥቶ ሲያርፍ በዛው የሞተ ይመስላል፡፡ ዴላኒ ጃኬቱን ገልቦ ከማየቱ በፊት ወደከበቡት ሰዎች ዞር ብሎ –

-ለመሆኑ የነካው አለ? በአጋጣሚ ማለቴ ነው አለ።

ሁሉም በዝምታ በአንድ ላይ ራሳቸውን ግራና ቀኝ ነቀነቁ።" ገጽ213

ሰርጀንት ዴላኒ ከገለታ ኪስ ውስጥ ያገኘው መታወቂያ "በቀለች" የሚል ስም ነበረው። (ገጽ 215) ይህ የገለታ አስከፊ ዕጣ ፋንታ (ማንነቱ ሳይታወቅ መቀበር) እዚህ ላይ በጣም አሳዛኝ ቢሆንም አዳም ግን ሌላ መጽሐፍ ላይ ለገለታ alternative and better ending ማበጀቱ ደስ ብሎኛል። አንባቢዎች Addis Ababa Noir የተባለው መጽሐፍ ላይ "Of Buns and Howls" የተባለውን የአዳምን በገለታ ላይ የሚያጠነጥነውን በእንግሊዘኛ የተጻፈውን ታሪክ እንድታነቡ አበረታታለሁ።

ዴላኒ የገለታን ሬሳ በመመርመር ላይ እያለ የገለታ ዲምፕል ስላስገረመው ሰርባዳውን ቦታ በአመልካች ጣቱ ነካው። የዛን ሰዓት የገለታ ዲምፕል ከገለታ ላይ ተላቅቆ እየተንሳፈፈ ተነስቶ እየተፈረፈረ በንኖ ጠፋ። (ገጽ 216) ገለታ ሥጋው ሲሞት ዲምፕሉ፣ የማንነቱ ዋነኛ ምልክት፣ መለያው፣ his essence፣ ልክ ነፍስ ከሥጋ ተለይታ ትመጥቃለች እንደሚባለው ከገለታ ላይ ተንሳፍፋ ተነስታ የሰርጀንት ዴላኒን ነፍስ እንደተዋሃደች እናነባለን። ሰርጀንት ዴላኒ ቤቱ ገብቶ ጠዋት ከእቅልፉ ነቅቶ በመስታወት ፊቱን ሲመለከት የገለታ ዲምፕል ፊቱን አስውባዋለች። “በማያውቀው ምክኒያት ጉልበትና ዐዲስነት ተሰማው። ..,.ዩኒፎርሙን ለባብሶ ሲወጣ የሰፈሩ መንገድ ገና ከእንቅልፉ አልተነሳም፡፡ ገጹ ብቻ አይደለም የተለወጠው፣ ከአካሄዱም ከዕድሜውም አሥር ቁጥሮች የቀነሰ ወጣት መስሎ ነው። (ገጽ 219)

ይህ ታሪክ ለኔ የአፍን ጉልበት አሳይቶኛል። ዴላኒ በመልኩ በጣም ተከፍቶ፣ የሆነ ጊዜ ለእግዚያር እንደ ጸለየ እናነባለን።

"እግዜር ወደ ቀጭን ቆንጆ ለውጦ ደደብ እንዲያደርገው መአት ጊዜ ለእግዜር ጸልዮአል:: ለዚህ ሁሉ እሱን መሰል ዙሉዎች ደህና ምንጭርና ቦርጭ ሰጥቶ ለምን አምላኩ እሱን ነሳው? (ገጽ 206 – 207)

እዚህ ላይ “speaking things into existence” የሚለው አገላለጽ ሠርቶ ይሆን? ...ምናልባት በልቡ የተመኘው እና በአፉ የጸለየው እውን ሆኖለት ይሆን? የገላታ ዲምፕል (ማንነት፣ ነፍስ) ዴላኒ ውስጥ መሥረጹ እና መገለጡ ድባቴ ውስጥ የነበረው ዴላኒን ዐዲስ የሕይወት መንገድ ከፍቶለታል። የአገራችን ሰው ከአፍ የሚወጣን ቃል ጉልበት ለማሳየት አንድ ሰው ስለሞት እንኳን ካወራ 'ሟርተኛ' የሚል ስም ይሰጡታል። ምክንያቱም ያሟረቱትና የተናገሩት ይደርሳል ተብሎ ስለሚታሰብ። ይህ አዎንታዊ ፍላጎቶቻችንም ላይ ይሠራል። (thought become things or what you think and speak you become) የዴላኒ እናት ደሞ ከመሞቷ በፊት የመጨረሻ ከአፏ የወጣው ቃል ምርቃት ነበር።

"እናቱ የሚያምር አፏን ለመጨረሻ ከመዘጋቷ በፊት የተናገረችው ትዝ ይለዋል፡ .... ʻልጄ ኑሮህ ሰላም ይሁን፡፡'" ገጽ217

የዴላኒ ዐዲስ ጉልበት ማግኘት፣ ድባቴ ተራግፎ የዐዲስነት ስሜት መሰማት እና የውስጥ ሰላም ማግኘቱ እውነትም ለዴላኒ የእናቱ ምርቃት ሠርቶለታል ያስብላል።

'ቅልልቦሽ' የተባለው የቀርካሃ ዋሽንት ፊልም እናገለታ (Magical realism and synchronicity 4)

ስለ ገለታ ስንወያይ የልጅነት ጓደኞቹ የት ደረሱ የሚለውን መጀመሪያ ብንዳስስ ጥሩ ነው። ባካፋ የባንክ ሠራተኛና የኮስሜቲክ ነጋዴ ቢሆንም ሕልሙ ፊልም ፕሮዲውሰር መሆን ስለነበር 'ቅልልቦሽ' የሚል ፊልም አቀናብሮ ለእይታ አቅርቧል። ዘሪሁን ማፏጨት ይወድ ነበር። ባካፋ እና ዘሪሁን በመተባበር እዚህ ፊልም ላይ የተደረሱት ሙዚቃዎች በዘሪሁን የፉጨት ድምፅ ተቀናብሮ ቀርቧል። ፊልሙ ላይ ከሚተውኑት ሰዎችመሃል ፊቷ ባይታይም በአለባበሷ እና በአጋጌጧ ጌርሳሞትን የምትመስል ተዋናይ እናያለን።

ተረበኛውና ብስጩው አቡ(ራሚሱ) ከማያፈቅራት፣ አሥራት ከምትባለው ውሽማው ጋር እየተዳራ ይህንን ባጋጣሚ እጁ ላይ የገባውን ፊልም ይመለከታል። የፊልሙ ማስታወሻነት ለገለታ፣ ለአቡ (ራሚሱ)፣ ለጌርሳሞት እና ለሌሎች የጣቦት ማደርያ ልጆች ይላል።

ከዚህ በታች የምንወያየውን ፊልም ፕሮዲውስ ያደረገው ባካፋ መዝገቡ ነው። ይህንን ፊልም የምናየው አቡ (ራሚሱ) ፊልሙን ባየበት ዓይን ቢሆንም የፊልሙ ፕሮዲውሰር የመጨረሻ ትዕይንቱን በያዘው ረቂቅ ወይም ቢጋር ላይ ያሰፈረውን ሐሳብም እያጣቀስን ይህ ፊልም ከገለታ ጋር የተያያዘበት መንገድ እናያለን።

In this section, I’ll show how magical realism enters quietly, through layers of hidden meaning. አዳም beautifully weaves strange coincidences and subtle patterns into the fabric of ordinary life—never calling attention to them, yet letting them echo across time and memory. While the characters remain unaware, the reader glimpses a quiet synchronicity unfolding beneath the surface. It’s a delicate, masterful touch—the world stays familiar, yet something deeper pulses through it, as if the past still whispers through the present.

የፊልሙ ታሪክ ስለ አንዲት የቀርከሃ ዋሽንት ነው። መኩሪያ የተባለ በፓዊ የገጠር ከተማ ውስጥ የሚኖር አንድ ገበሬ ዋሽንት ሠርቶ ሕይወት ለተባለች የዘመዱ ልጅ ሊሰጣት ከከተማው ምሥራቅ ጠርዝ ወደ ምዕራብ ጠርዝ ሲሄድ ገበያ መሃል ይጠፋበታል። በዚህ ምክንያት ይህ ሰው (ልክ ከጠዋቱአንድ ሰዓት ተኩል ላይ በጣም ይበሳጫል)። ይህች ዋሽንት ባለቤቷ ከጣላት ሰዓት ጀምራ የተለያዩ ሰዎች እያገኟት ግን በተለያየ ቦታ እየረሷት በሰባት ሰዎች ሥር ስትቀላለብ ከርማ (ጠዋት ላይ ልክ አንድ ሰዓት ተኩል ሲል ) አንድ የብስክሌት የፊት ጎማ ዋሽንቷ አጠገብ መጥቶ ቆመ:: የጃኬቱ እጀታ ብቻ የሚታይ አንድ እጅ አነሳት……ካሜራው ብስክሌትና ሊጋልባት በመሳፈር ላይ ያለ አንድ እግር ብቻ ያሳያል፡፡ ተሳፋሪው ጀርባ ላይ ባክፓክ አለ፡፡ የተሳፋሪው ፊቱ ወይም ፊቷ አይታይም፡፡ የባክፓኩ የላይኛው ኪስ ላይ ዋሽንት ተሸጣለች፡፡ ገጽ 203

ስርጉድ ቀዳዳዎቿ ያዝ ለቀቅ ሲደረጉ ውብ ድምፅ የምታወጣው ዋሽንቷ ከምሥራቅ ጠርዝ እስከ ምዕራብ ጠርዝ ስትጓጓዝ እንደጠፋችው፣ ድምፁ የሚያምረው ጉንጨ ስርጉዱ፣ ዲምፕላሙ ገለታ ሕይወቱን ለማሳካት ወደ ሩቅ አገር ተሰድዶ ሕይወቱ ያለፈ ወጣት ነው።

ገለታ በሕይወት እያለ በተደጋጋሚ፣ ተመሳሳይ ስዓት (ከጠዋቱ1.30) ላይ የሚያልቅ ሕልም ያይ ነበር። ሕልሙ ላይ የነበረው ድምፅም (ዲድ ኤኒ በዲ ተች ዚስ ጋይ? (ይሄን ሰው የነካው አለ?) የሚል ነበር። ይህ ጥያቄ ሰርጀት ዴላኒ የገለታ ሬሳ አጠገብ ቆሞ የጠየቀው ጥያቄ ነበር።

የፊልሙ መጨረሻ ላይ ዋሽንቱን ያነሳው ሰው ፊቱ ወይም ፊቷ አይታይም ሲል፣ ሴት ወይም ወንድ ይሁኑ አይሁኑ አይታወቅም የሚል ሃሳብ ይጠቁማል።

በገጽ 215 ላይ ሰርጀንት ዴላኒ የገለታን መታወቂያ ሲመረምር ጾታው ወንድ ቢሆንም መታወቂያው ላይ ግን የሰፈረው ስም 'በቀለች' እንደሚል አጣራ። The fact that the last person to pick up the flute has an ambiguous identity, echoing the gender confusion on the deceased ገለታ's ID is so intriguing.

ከፊልሙ ቢጋር:- የዋሽንቱ ቀለም፣ ካሜራው የዋሽንቱ አፎችላይ ማተኮሩ ... ዋሽንቱ አጠገብ ያለው ሳር ... ፊልሙን ያጀበው የፉጨት ሙዚቃ…

"ፀሐይ እንደ ወጣች። ዋሽንቷን ከእርቅት እናያለን፡፡ (ቢጫ የመሰለ ቀለም) ስላላት ከአስፋልቱ ጥቁረት ጋር በንጽጽር ጎልታ ትታያለች፡፡) ካሜራው በትንሽ ከባቢ ውስጥ ማታ ላይ ዋሽንቷ በወደቀችበት ሥልት:: (አጠገቧ ያለ ሳር በነፋስ ይነቃነቃል)። (ካሜራ (ዋሽንቷን በተለይ ቀዳዳዎቹን ወይም የዋሽንቱን አፎች ያለ አውድ ያሳያል)፡፡ የጠዋት ነፋስ ገኖ ይሰማል፡፡ በቀዳዳዎቹ ነፋስ ሲያልፍ ይሰማል ዳንቴል' የተባለው የፉጨት ድርሰት እዚህይገባል፡፡ " ገጽ 240

ገለታ የሞተበት ቦታ እና የፊቱ ገጽታ:- ዓይኖቹ ሳሩን የሚያዩ መምሰላቸው... ልክ እንደ ዋሽንቱ አፉ ላይ ትኩረት ተደርጓል... በዋሽንቱ ቀዳዳ ንፋስ እንዳለፈው የገለታም ስርጉድ (ዲምፐል) በነፋስ እንደተነሳ ዓይነት ከጉንጩ ተላቆ በንኗል፣ ቀኝ እጁም ያረፈበት ቦታ የዋሽቱን ቀለም የሚመስል ቢጫ አበባ ላይ ነበር...

"ከፊት ለፊቱ ቀጫጫ ወጣት ያናወዘ መስሎ በጀርባው ዛፍ ተደግፎ መሬት ላይ ተቀምጧል፡፡ ........ (ዐይኖቹ ጭኑ አጠገብ ያለ ሳር የሚያዩ ይመስላሉ)።.... በከፊል ተከፍተዋል፡፡ (ቀላ ያለ ልጋግ በአፉ ቀኝ ደርዝ ፈሶ ወጥቶ አገጩ ላይ ደርቋል)፡፡ ..... ዛፎቹ ሥር የልጁ ቀኝ እጅ አረፈበት ድረስ ቢጫ አበባ ያላቸው ሱዛናዎች ይንቦገቦጋሉ፡፡ ምናልባት ለክብሩ ወይ ለቅሌቱ ነው::"ገጽ 240

ፊልሙ:- "ከዛ ፉጨት ይጀምራል፡፡ ፉጨቱ ፊልሙ ሲጀምር የነበረው የላሎ ሽፍሪን ሙዚቃ ነው":: ገጽ 203

ፊልም ቢጋር:- “ዳንቴል' የተባለው የፉጨት ድርሰት እዚህይገባል”። ገጽ 240

የገለታ ሬሳ አጠገብ ቆሞ ሰርጀንት ዴላኒ ማፏጨት ይጀምራል።

"ልብ ሳይለው የልጅነቱን አንድ ዘፈን መዝፈን ጀመረ፤ በቀስታ እያፏጨ፡፡ ሦስት ሜትር ከእሱ የራቁ ሰዎች ድምፁን ባይሰሙም አፉ በማሞጥሞጡ እያፏጨ እንደሆነ ይገባቸዋል፡፡ ጨዋ ድርጊት ባይሆንም ግድ አልሰጠውም"፡፡ ገጽ 215

ፊልሙ:- እዚህ ፊልም ላይ ሰባት ሰዎች ከተቀላለቧት በኋላ ዋሽንቷን መጨረሻ ላይ ቀልቦ የወሰደው ሰው ማንነቱ በሌሎች የማይታወቅ ነበረ። የዋሽንትቷ ዕጣ-ፈንታ ቀጣይ ነው።

ገለታ ሲሞት የማንነቱ፣ his entire essence የሆነው ዲምፐሉ ቤተሰብና ወዳጆች በማያውቁት በሰርጀንት ዴላኒ ተወርሷል። የገለታ ሕይወት በዴላኒ ዐዲስ ማንነት ውስጥ ይቀጥላል። "ዋሽንቱም አልጠፋም ቦታ ነው የቀየረው"። ገጽ 243

ባካፋ የደረሰው እዚህ ፊልም ላይ የእዚህን ድርሰት ቁልፍ ሐሳብ ሲገልጽ እንዲህ ይላል:-

"በነገራችን ላይ ይሄ ፊልም ቀጣይ ክፍል አለው:: የቀጣዩን ክፍል ስክሪፕት ድራፍት ቢጋር አይተነዋል፡፡ ይሄ የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ሁለተኛው ክፍል የሚበቅልባቸው ዐይኖች ስላሉ እንዳይጠፉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ለፊልሙ አርታኢ ደጋግማችሁ አስታውሱት፡፡

ምክንያቱም ጐጦቹ ዐይኖቹ ለቅብብል የተሰሩ ላይመስሉት ይችላሉ፡፡ ይሄ ፊልም የራሱ አጨራረስ ቢኖረውም የሚቀጥለው ፊልም የሚጀምርበትን ጥሬ ሃብት ተሸክሞ ይመጣል፡፡ ቀላል ምሳሌ ልውሰድና፡ ዋሸንቱን ከወደቀበት ማን አነሳው? ከዛስ? ይሄ አጨራረስ ራሱን የቻለ ጉጥ ወይም ዐይን ነው:: ድርሰቱ ገላ ውስጥም ትንሽ ቢኮረኮሩ የሚፈኩ ዐይኖች አሉ፡፡" ህዳግ ገጽ 242

***መውጫ***

የዚህ የመጽሐፍ መጀመሪያ ገጽ ላይ ከርዕሱ ሥር (ሥግር ልብወለድ) ይላል። እንደማንኛውም አንባቢ ሥግር ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ አዳም "ሥግር: በሕጽናዊነት" በሚል ርዕስ ይህንን ጉዳይ በጥልቅ ያብራራበትን article አስሼ ገጽ 10 ላይ ይህንን አገኘው እናም ለእናንተ መጽሐፉ ላይ ያገኘሁትን ይህችን ነጥብ ላጋራችሁ ወደድኩ።

"ነባሪው አለም ድኅረዘመናውያን ወይም ድኅረመዋቅራውያን እንደሚሉት ድርሳን (ቴክስት) ብቻ አይደለም፡፡ እውነተኛው ቁስአካላዊው ዓለምና በማስተማሰል የተፈጠረው የድርሰት ዓለም አሉ፡፡

ሐሳባችንም አለ (ደራሲው ማለት ነው)፡፡ አንድን ድርሰት ሥግር መስራት ማለት፣ ከድርሰቱ ውስጥ የሆነ ኩነት(event) ወስዶ ወደ ተፈለገው ወይም ወደ ሚቻልበት እልፍ አቅጣጫዎች ወስዶ ድርሳን ወይም ድርሳኖች መፍጠር ማለትነው:: በድርሳን ውስጥ ሁሉ ነገር ኩነት ነው:: ለምሳሌ፡- ዝምብሎ የተቀመጠ ወንበር በራሱ ኩነት ነው፡፡ ኩነት የልዋጤ ባህርይ ነው) በአንድ ነጠላ የመሰለ ጉዳይ ውስጥ ብዝሃነት (multiplicity) ወይም ያልተከፈተ እምቅ ኃይል (ፖቴንሽያል) አለ፡፡ መሆን (becoming) ማለት አንድ ነገር፤ ሁኔታ ሐሳብ ወይም ኩነት በወሰን አልባነት ሲተረተር ወይም በሥልት ለተለያየ አገልግሎት ሲከፈት ማለት ነው:: ሁልጊዜም 'አላቂ' ተብሎ በተሰየመ ጉዳይ ውስጥ ከወሰን የለሽነት ጋር እንግጣጠማለን። 'በአንድ ጥሬ የእብነበረድ ሰሌዳ ውስጥ ኅልቁ መሳፍርት እምቅ ነገር አለ እንዳሉት አዋቂዎች። የዕብነበረድ ሰሌዳው በተለያዩ ባለሙያዎች:- በቀራጩ፣ በቤት ሠራተኛው፣ በሠዓሊው፣ በደራሲው፣ ዘመድ በሞተበት ወዘተ የተለያየ መልእክት ወደአላቸው ነገሮች ሊለወጥ ይችላል፡፡

ኩነት እንደ ፈላስፋው ሌይብኒዝ አባባል አንዲት ነጥብ ፅንፍ የለሽ ሂደቷ ለአፍታ ሲቋረጥ ነው:: በአጭሩ ኩነት መርጠን ይሄንንም በአፍታ ግታት(finite interruption) ከእምቁ ሃይል እምብርየለሽ (Infinite) መስከ መፍጠር ማለት ነው:: ያ እምቁ ኃይል በሁኔታዎችና በነገሮች መሃል ያለው የማያልቅ ግኑኝነት (የአለፈው፣ የአሁን፤ የሚመጣው) ወይም ትስስር ነው። እያንዳንዱ ደርሳን በግኑኝነት መርበብት ውስጥ የተጠመደ ነው: በነበሩት፤ ባሉትና በሚመጡት። እንደውም ባልነበሩት) ያልነበረው ገና የሚጠበቀው ቴክስት በደራሲው በቦርገስ

ሃሳዊ ቴክስት(pseudo-textuality) ይባላል፡፡ ይሄን 'አፍ' የተባለ ልብወለድ ወደ አንባቢ-ደራሲ ስወረውር ('እንካ' ስል) እነዛ ሃሳዊ ቴክስቶች በየቦታው ይኖራሉ ብዬ ተስፋ በማድረግ ነው::" ገጽ 10

ስለዚህ አዳም እዚህ ድርሰት ውስጥ የተካተቱት ገጸ-ባህሪያት በሙሉ ያልተከፈተ እምቅ ኃይል (potential) እንዳላቸው ስለሚያምን ከዚህ መጽሐፍ አንዱን ገጸ-ባህሪ ወስዶ የሕይወት እስትንፋስ እፍ የሚልበት ጸሐፊ ምንኛ የታደለ ነው!

So አፍ for me is a book that cements the idea of how an ordinary world can be transformed into something much more profound when viewed through the lense of metaphor and surrealism.

Adam creates a sense of synchronicity throughout the narrative by connecting each character through magical realism, drawing on dreamlike and nostalgic events—where time and memory blur, where past and present fold into each other, and where characters don't just intersect, they echo one another in meaningful, perhaps even mystical, ways. In my view, Adam uses this book to liberate our imagination, embracing the irrational and the absurd, while exploring the continuity of life and inviting us to engage with the mysterious dimensions of human experience.

በእውነት ኦ አዳም ብዬ አፌን ከፍቼ የቀረሁበት መጽሐፍ ነው።

ምክር ለአንባቢዎች :- ከ'አፍ' ውስጥ ዕንቁውን ፈልቅቆ ለማውጣት መጽሐፉ ሁለቴ ቢነበብ ጥሩ ነው እላለሁ።